# ለአዋጁ አዋጅ

በየጊዜው  የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የሁለተኛ ደረጃና የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ከጠቅላይ ግዛት ጓደኞቻቸው ጋር በመተባበር አድኃሪውን መንግሥት በተለያዩ የሕብረተሰብ የኑሮ ዘርፎች ላይ የሚፈፅመውን አምፅ በአንድ ድምፅ ያወግዛሉ። አሁንም በማውገዝ ላይ ናቸው።

አድኃሪው መንግስትም በተራው በቀናት የሚቆጠረውን እድሜውን ለማራዘም በመንቃት ላይ ያለውን የኢትዮጵያን ገበሬና ነጋዴ እንዲሁም ሌላውን ሞያተኛ ሕዝብ በዘር፣ በሃይማኖትና በቅርብ በተፈለሰፈው በዕድሜ በመከፋፈል ጆሮውን በሃሰት ፕሮፓጋንዳ በማደንቆር ላይ ነው።

እንደተለመደው ሁሉ የአገር ግዛት ሚኒስቴር ከንቱ ማስፈራሪያ፣ እንዲሁም የፖሊስ ድንፋታ ሲያልቅ የሀገሪቱ መሪ ማብራሪያ ይሠጣሉ። እስኪ የዘንድሮውን ንግግር በመተንተን የትኛው ወገን ከልብ ለሃገሩ  እንደሚያስብ በእንጀራ ላልተገዛውና በግልፅ ለማየት ለሚችለው ማብራሪያና ማሳሰቢያ እንስጥ።

ጃንሆይ በንግግራቸው መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ሊያራምደው የሚችል ኃይል ትምህርት መሆኑን ያምናሉ። እኛም በዚህ እናምናለን። ችግሩ የሳቸው እርምጃና የኛ የተለያየ መሆኑ ነው። እንደተረዳነው የሳቸው አስተሳሰብ ጥቂት ፀሐፊዎች/ወንበር አሟቂዎች/ ፣ ጥቂት ቴክኒሻኖች በዚያ ላይ ብዙ ስምና ዝና ነው። የኛው ይህ አይደለም። እኛ የምንለው እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመማር መብት አለው ነው። መማር ማወቅን ስለሚያመለክት የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን  /ሌላ ኃይል ሳይነግረው/ እራሱ አመዛዝኖ በሚፈልገው መንገድ ባሰኘው ፍጥነት መራመድ አለበት ነው የምንለው። ያለዚያ ጭብጥ በማይሞሉ ሰዎች የኢትዮጵያ የወደፊት ርምጃና ዕድል በአሜሪካን መንግሥት ዕርዳታ ሊወሰኑ አይችሉም! አይገባቸውም።

እዚህ ላይ ጃንሆይ ዘንግተውት ቢሆን የራስ ካሣን ምክር እናስታውሳቸው "ተፈሪ ይኸን የድሃ ልጅ አታስተምር ኋላ ራስህ ላይ ይወጣል" የትምህርትን ውጤት ካሣ በይበልጥ አውቀውት ኖሯል!! ጃንሆይ ስለትምህርት መስፋፋት ሲናገሩ "በባላገርም ሆነ /በከተማ / ከመማር የተነጠለ ማን ይገኛል? ብለዋል። "ይህ መችም ተጨፈኑ ላሙኛችሁ" ነው። ከ ሃያ ሁለት ሚሊዮን ሕዝብ ሃይ አንዱ ፊደል አለመቁጠሩን ማንም ስለሚያውቀው ይህን ማስተባበል ጊዜ ማባከን ነው። ቀጥለውም ትምህርትን ለማስፋፋት ያደረጉትን ጥረት ከደረደሩ በኋላ "ሕዝባችን ረድቶናል" ሲሉ ደምድመዋል። "ሀ" ሲባል ጀምሮ የተማሩትን የኢትዮጵያ ወጣቶች ላቡን እየጨመቀ በመኖር ጠርዝ ላይ ተንጠልጥሎ ያስተማረው ማን ሆነና? የኢትዮጵያ ሕዝብ በረዳትነት ደረጃ ተሰለፈ? ይህም "ተጨፈኑ" ነው።

የታህሣሥ ደም ቢያቃዥዎት የለቀቁትን ቤት ሰጠሁ እያሉ ከሚመጻደቁ/ለማስመለስ ነው እንጂ ግምተዎን ወስደዋል/ ነድመው ከሆነ ሊወስዱት ይችላሉ። ሃብትነቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑ ቀርቶ የርስዎ ከሆነ ማለታችን ነው።

የመንግሥቱ አቋም ስለማይፈቅድ ተማሩ የሚባሉት ኢትዮጵያውያን ሁሉ ተገቢ ቦታቸውን ባለማግኘታቸው ሕዝባቸውን ሊያገለግሉ አልቻሉም። አሁን ብዙዎቹ የሚሰሩት የፊርማ ሥራ ያለብዙ ችግር/እንደብዙዎቹ ከፍተኛ ባለሥልጣኖቻችን /በቄስ ትምህርት ሊያካሂዱት ስለሚችሉ ይህ ሁሉ "ጥረት" ባላስፈለገም ነበር።

ጃንሆይ የወጣቶችን ትኩስ ስሜት አውግዘዋል። ግን ጊዜው ራሱ ትኩስ መሆኑ፣ በዕድሜ ብዛት ይሆናል ያልተሰማቸው!!

ያለንበት ሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሩጫ ዘመን ነው። ለባላባታዊና ተንፏቃቂ መንግሥት ቦታ የለውም። ተግባባን? ስለዚህ ተጠንቶ የተደረሰበት እንጂ ጃንሆይ ተጽፎላቸው እንዳነበቡት የስሜት ጉዳይ አይደለም።

ጃንሆይ ንግግራቸውን በመቀጠል ሳናመዛዝንና ሳንገምት የምናደርገው ርምጃ አይኖርም ብለዋል። ሁለትና ሦስት ወራት በመቶ ከሚቆጠሩ አወዳሾች ጋር አገር ለአገር ዙረት እንደገና ለውጭ እንግዶች/ የኛ እንግዶች/ በኢትዮጵያ ምድር የሻምፓኝ “የመልስ ምት” መቶ ምናምን አምባሳደሮች እንዲህ አድርጎም ማመዛዘን የለ!!

ስለዕድገት ስያትቱ “በእግዚአብሔር ቸርነት አሁን ካለንበት ደረጃ አድርሰነዋል ብለዋል። እዚህ ላይ ተገቢው ጥያቄ ከየት ተነስተን ነው? ጣሊያን በሰራው መንገድ መንሸርሸር ተችሏል።

በብድር ገንዘብ በተሠሩ አውሮፕላን ጣቢያዎችም በዱቤ የተገዙና በልመና የተገኙ አውሮፕላኖች ያርፉሉ። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የበጐ አድራጐት (የንግድ) ድርጅትም ብዙ የቢራ ፋብሪካዎችን አቋቁሞ በመጠጥ በኩል ርምጃችንን አፋጥኖልናል። ይኸው ድርጅት ለሃብታሞች መታከሚያ ጥቂት ሃኪም ቤቶችን ከፍቷል ። በተጨማሪም ሕዝብ እንደ ከብት እየታጐረ የሚመላለስባቸው ባለአንበሣ አውቶብሶችንም ገዝቶልናል። ግሩም ድንቅ የንግድ ሙያ!! አዲስ አበባ ሳትወዛ የጠቅላይ ግዛቶችን ደም እየመጠጠች አንዳንድ ሕንጻዎች ተሠርተውባታል። ይህ ማንን ጠቀመ? ከግንባር ላይ ሃብታሞች በሠሩዋቸው ቤቶች የተከለሉት የሣርና የጭቃ ጐጆዎች ከትኋንና ከቁንጫ ጐሬነት መቼ ዳኑ? እናንተ ገዥዎቻችን ስለደላችሁ እኛ የተጠቀምን መስሏችሁ ይሆን? ሃሰት ነው እናንተ የበላችሁት እኛን አያጠረቃንም።

አዬ ጉድ! አያችሁት የሃምሳ ዓመት ሥልጣኔአችንን ። ኢትዮጵያ ከታናናሾቿ የአፍሪካ ሀገሮች በኑሮ ደረጃ የመጨረሻይቱ መሆንዋም ተዘነጋ። በትምህርትም እንደዚሁ የመጨረሻይቱ መሆኗ ተዘለለ። ይህን ሁሉ ማን ይናገር ? ሁሉ ታፍኖ። ኧረ ይብቃን? <u>ሲከር ይበጠሳል</u> ለአዲስጌ ፣ለሞጃ፣ለቡልጌ እንዲሁም አንዳንድ በጋብቻና በአበልጅነት ለተሳሰሩ ለሐረጐት ፣ለቤክሪ፣ለጆቴ፡ለዮሐንስና ለቀሩት ጥቂት ቤተሰቦች ድሎት ሃያ አንድ ሚሊዮን የኢትዮጵያውያን መሰቃየት ይገባቸዋልን?

እግርማዊነታቸው ንግግርም ውስጥ “ፕሮብሌሞች መፈጠራቸው የማይቀር ነውና መፍትሔው የሚገኝላቸው በሕብረተሰቡ አርቆ አስተዋይነት “ ነው። የሚልም ይገኝበታል። እዚህ ላይ ሕብረተሰቡ የቱ ነው? በኢትዮጵያ የመሬት ክልል ውስጥ ያሉትን ስበአዊ ፍጡሮች ለመግዛት የተመረጠው  የገዥው ክፍል ነውን? ወይስ ሌላውም የኅብረተሰቡ አባል ነው? እንደግርማይነታቸው አነጋገር ኅብረተሰብ ማለት ገዥዎች ማለት ብቻ ነው። ይህ አጠራርም ። ሌላው መች ተናግሮ? እንዴትስ ሃሳቡን ገልጾ? ለመሆኑ ለሃገራችን ፕሮብሌሞች መፍትሔ እየተባሉ የሚነገሩን ነገሮች የሚላኩልን የገዥዎቻችን ደጋፊና ተባባሪ በሆኑት በነዚያ ከባሕር ማዶ ባሉት አማካሪዎቻችን አይደለምን?

ምንም አለመሠራቱን በመረዳት ጥያቄ ያቀረቡትን ጒልማሶች ለመዝለፍ በመቃጣት “እጅግ አስቸጋሪና የተወሳሰቡትን ሶሻልና ኢኮኖሚና ፖለቲካ ነክ የሆኑትን ጉዳዮች ትምህርት ሳይፈጽሙ” ባልበሰል አዕምሮ “ሊተነትኑ መሞከር ነውር መሆኑን በመግለጽ ለኢትዮጵያ ችግሮች መፍትሔ የሚያስገኘው የጃጀ አዕምሮ መሆኑ በግልጽ ታውጇል። ባለሦስት ሃምሳ ዓመታት ፕሮብሌማችን እያደረ ሲውሰበሰብ እንጂ ሲፍታታ አልታየም። በአባቶቻችን ደም የተጠበቀው ነፃነታችን በገዥዎቻችን ተገፈን ሀገራችንም ለአሜሪካኖች ተሸጠች። እነሱን ለማስዎጣት ሌላ ጦርነት እንደሚያስፈልገን አላሰቡትምን? ጃንሆይ! ትዕግስታችን እስከ መቼ ነው? በሙሉ ኢትዮጵያ እስክትሸጥ? ደሃው ኢትዮጵያዊ እኮ ወደ ውጭ ሃብት አላሸሸም!!! ሃገሪቱ ተሸጣ ስታልቅ የትም ሄዶ ለመቀመጥ።የአድሃሪውን መንግሥት የተቃወመ ሁሉ “ያልበሰለ አዕምሮና ያልተመዛዘነ አመለካከት ”አለው ቢባል በስተርጅና መዋሸት አይሆንም?? ያውም ላይታመኑ?

በገዢንና በተገዢ መሃል የአባትና የልጅነት መተሳሰብ አለ የሚለው ሃሳብ ከሞተ ሰባት መቶ ዓመታት ስላለፉት መደገሙ ይገርማል።

ከግርማዊነታቸው ንግግር እንደተረዳነው “የውጭ እጅ” የሚፈራ ይመስላል። ከአሜሪካን እጅ በስተቀር ሌላው አይጠቅምም። የአሜሪካን እጅም የውጭ አይደለም። ኢትዮጵያ ሃምሣ ሁለተኛይቱ

የተባበሩት የአሜሪካን እስቴቶች አንዷ ስለሆነች ! ደግሞስ የአሜሪካን መንግሥት ከመዳፉ ሥር አኑሮ እሚገዛት ሀገር ውስጥ ሌላ የባዕድ እጅ እንዴት ሊገባ ይችላል? በማይታመን ወሬ የሕዝቡን ሃሳብ ማደፍረስ ከእንግዲህ የሚቻል አይመስለንም። ይብቃ! ገዢዎቻችን ከተራው ኢትዮጵያዊ የተወለዱት ተማሪዎች ደፍረው ነውራችሁን ሲናገሩ መታገሳችሁ መጠቀሱ ምንም አልነበረም። ነገር ግን ፖሊስ፣ ጦር ሠራዊትና ክቡር ዘበኛ በሕዝብ ላይ ሲዘምት "የሕዝቡን ደህንነት " ለመጠበቅ ነው የምትሉት የኢትዮጵያ ሕዝብ ማለት አድስጌና ሞጃ ብቻ መሆኑ ነውን?

በጣም የሚደንቀው የሕዝቡ ክፍል አካል እንደመሆናቸው መጠን ለሕዝቡ መብት የሚከራከሩትን ተማሪዎች ሲደበድቡ ሕዝቡ እንደሚተባበር  የሚተማመኑ መሆኑን መገለጹ ነው። ጃንሆይ ንግግራቸውን በመቀጠል "ሳናመዛዝንና ሳንገምት" የምናደርገው እርምጃ አይኖርም ብለዋል። ለውጭ እንግዶች በኢትዮጵያ ምድር ድግስ ማድረግና መስከር፣ ሰክሮም በፈንጠዝያ ተኩስ ደክሞ አዳሪውን ከዕንቅልፉ ማባነን ?  አያሌ ኤምባሲዎችን ማቋቋም-ለወሬና ለዝና ሲሉ!!!! የመቃብር ደንጋይ በሃያ ሁለት ሚሊዮን ብር ማሠራት፣ ውጭ ሀገር ፋብሪካ ማቋቋም፣ አሜሪካን ሀገር ሄዶ ለአንዱ ዩኒቨርስቲ ዘጠኝ መቶ ሺህ ብር መቸር፣ የኢትዮጵያን መሬት ለራስ ለተዋለደና ለተዛመደ አከፋፍሎ ደሃውን ከምርቱ ከአራት ሶሥት እጁን በመዝረፍ የደም ዕምባ ማስለቀስ.........  ወዘተረፈ............እንዲህም አርጐ ማመዛዘን የለ።

እግርማዊነታቸው ንግግር ውስጥ፤ ይህ አሁን የተፈጠረው ሁኔታ በይበልጥም የሚያሳስበን ቀደምት አድርገን የምንመለከተውንና ለሕዝባችንም ያቀድነውን የትምህርት ፕሮግራም በማይገባ በማስተጓጐሉ ነው። የሚል አንቀጽ አለ። እኛም እኮ ትምህርት ለአብዣኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳይዳረስ የሚያደርጉት እንቅፋቶች ይነሱ ነው ያልነው። ትምህርት ቀደምትነት ሊሰጠው እንደሚገባ በማመን ነው።አካለ ወልድን የሚያክል ድፍን ቅል እየመራው ትምህርት ሊስፋፋ አለመቻሉን በመገንዘብ ነው፡ የሱን መነሳት የጠየቅነው።  መምህራንን በመሳደብና በማንጓጠጥ፣ ዕድገታቸውንም በመቃወም እያበሳጨ ሲያባርር ? እሱ እያስተማረ ነው ትምህርት የሚስፋፋው?

ያለአግባብ ለኤምባሲዎች የሚወጣው ገንዘብ ተቀንሶ ለትምህርት ይዋል ሲባል ስለኤምባሲዎች ጥቅም እንዲያብራራ የተላከው ከተማስ ምን ይሆን እወዳጅ አገር በሄድ ጊዜ አንብቦ የመጣው? የትኛው ኤምባሲ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ በተሠሩ ዕቃዎች በመጠቀም የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ የሚያዳብረው? መጠጡ ነው? ልብሱ? ወይስ የቤት ዕቃው? አቶ ከተማ የኢኮኖሚክስ መጽሐፍ የመጀመሪያውን ገፅ ገልጦ ይመልከት። በተላኩ ቁጥር የሆነ ያልሆነውን መቀባጠር አይጠቅምም። ዕውነቱ ሲገለጽ ያሳፍራልና።

መንግሥት አጥፊ በሚላቸው ተማሪዎች ላይ እርምጃ እንደሚወስድ ተገልጿል። ይህን ሊያደርግ ከቻለ እንደማይተው በፊትም እናውቃለን። ለወደፊትም የሚደረገው ጥንቃቄና ጥናት የሚያስገርም አይሆንም።ችግሩ ጥናቱና ጥንቃቄው ለመሠረታዊው ፕሮብሌም መፍትሔ አለመሆኑ ነው። ግን አዎ ይገባል ከመሞት በፊት ያጣጥሯል!!

ከማክሰኞ ከመጋቢት አንድ ቀን ፲፱፻፷፩ ዓ.ም. ጀምሮ ትምህርት እንድንቀጥል ታዘናል። አሻፈረን!! ሲፈልጉ የሚያሶጡን ሲፈልጉ የሚያስገቡን የበረት ከብቶች መሰልናቸው? በኢትዮጵያ ሕዝብ ሃብት የምንማር ሙብትና ግዴታችንን የምናቅ ንጹህ ኢትዮጵያውያን ነን፡፡ለማሰብ እንችላለን የአዕምሮአችን ስለት ከዝገት አልተበላሸም። በኢትዮጵያ ሕዝብ ሃብት ጭብጥ የማይሞሉ ጨቋኞች ከአለቃቸው ከአሜሪካን መንግሥት ጋር የፈለጉትን ለማድረግ ይችላሉን? በፍጹም ከእንግዲህ ይህ ከንቱ ምኞት ነው።

“ለአገራቸው የታጩ የነገ ተተኪዎች” ይላል የማያረጀው ሐርግ! የፖለቲካና የኢኮኖሚ ነፃነት መጠየቅ ከሱቅ ዱቤ መጠየቅ አይደለም። ስለሆነም “ዱቤ ነገ” አጥጋቢ መልስ አይሆንም።ይኸ ነገ ስለራቀ ዛሬ መሆን አለበት።

የመጨረሻው ዓረፈተ ነገር “በብዙ ድካምና መሥዋዕትነት የተመሠረተው የኢትዮጵያ ዕድገት ያለአንዳች መሰናከል (ወደኋላ ሳይጐተት) እርምጃው ወደፊት እንዲቀጥል ማድረግ የሁሉ ግዴታ መሆኑም መዘንጋት የለበትም” ይላል። እኛ አልዘነጋነውም። ስላልዘነጋነው ነው እርምጃችንን ወደኋላ

የሚያስቀርብንን አድሃሪውን መንግሥት ከነቡቹሎቹና የአሜሪካን እጅ አዙር አገዛዝን ልንቋቋም የተዘጋጀነው።

አንባቢ ሆይ ! የእኛንና የመንግሥቱን አቋም ልዩነት መገንዘብ አያዳግትም። ተባብሮ የውስጥ ባላጋራን መቋቋሚያው ጊዜ አሁን ስለሆነ ትግሉን ከእኛ ጐን ተሰልፎ መቀጠል የእያንዳንዱ ንቁ ኢትዮጵያዊ ተግባር ነው።

ግንባር ቀደም የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች